## የዳንድይ ዎከር ሲንድሮም ምንድን ነው?

ዳንድይ ዎከር ሲንድሮም ከጽንስ የሚጀምር እና በአንጎል የኋለኛው ክፍል የሚገኘውና እንቅስቃሴን የሚቆጣጠረው ሰረብለም ተብሎ በሚጠራው እና እንዲሁም ዙሪያውን በሚገኘው በፈሳሽ የተሞላው ክፍልን የሚያካትት የአንጎል እክል ነው:: የዚህ ሲንድሮም ዋና ዋና መገለጫዎች የአራተኛው ቬንትሪክል (ማለትም በአንጎል እና በአከርካርዎች መካከል ፈሳሾች ያለምንም እንከን እንዲፈሱ የሚረዳ ጠባብ ቧንባ) መለጠጥ ፣ የሴሬቤላር ቬርሚስ (በሁለቱ ሴሬቤላር ክፍሎች መካከል የሚገኝ የአንጎል ክፍል) በከፊል ወይም በሙሉ ያለመኖር እና በውስጣዊ የአንጎል ክፍል ስር የዕጢ መፈጠር ናቸው:: በአንጎል ዙሪያ ያለው ፈሳሽ ያዡ ክፍል መጨመር እንዲሁም የግፊት (ፕሬዠር) መጨመርም መገለጫ ሊሆን ይችላል:: ስይንድሮሙ ሳይታወቅ ቀስበቀስ ወይም በድንገት ሊከሰት ይችላል:: በአብዛኛው በህጻንነት ጊዜ የሚከሰቱት ምልክቶች ዘገምተኛ የአእምሮ ሞተር እድገት እና በፍጥነት እያደገ የሚመጣ የራስ ቅል እድገትን ያካትታል:: ከፍ ባል ህጻናት ላይ ደግሞ በውስጠኛ የራስ ቅል ውስጥ በሚፈጠር ግፊት ምክንያት የሚከሰት ህመም ፣ ማስመለስ እና ኮንቩልሽን (ወይም ድንገታዊ የሆነ የጡንቻ መኮማተር) እና የሴሬቤላር እክል ምልክት የሆኑ እንደ አቅም ማጣት ፣የጡንቻ አለመቀናጀት ፣የአይን መንቀጠጥ ሊከሰት ይችላል:: ሌሎች ምልክቶቹ የጭንቅላት ዙሪያ መጠን መጨመር ፣ ከጭንቅላት የኋለኛው ክፍል እንደ እብጠት ያለ ነገር መውጣት ፣ አይንን ፣ፊትን እና አንገን የሚቆጣጠሩ ነርቮች ችግር እና ትክክለኛ ያልሆነ የአተነፋፈስ ስርአት ናቸው:: ዳንድይ ዎከር ሲንድሮም ብዙ ጊዜ ከሌሎች የሴንትራል ነርቨስ ሲስተም መዛባቶች ለምሳሌ የኮርፐስ ካሎሰም (በሁለቱ ሴሬብራል መካከል ያለ አገናኝ ክፍል) አለመኖር እና የልብ ፣ የፊት ፣ ክንድ ፣የእጅ እና የእግር ጣቶች ስነፍጥረት ችግር ጋር ተዛማጅነት አለው::

## ህክምና አለው?

የዳንድይ ዎከር ሲንድሮም ላለባቸው ግለሰቦች ያለው ህክምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተዛማጅ የሆኑትን ችግሮች ማከምን ያካትታል:: ትርፍ የሆኑ ፈሳሾችን ለማስወገጃ የሚጠቅም ልዩ ቧንቧ በጭንቅላት ውስጥ ማስገባት አንዱ መንገድ ነው:: ይህም በአንጎል ውስጥ ያለውን ግፊት (ፕሬዠር) ለመቀነስ እና እብጠትን ለመቆጣጠር ይረዳል:: ዳንድይ ዎልከር ሲንድሮም ያለባቸው ልጆች ያሉዋቸው ወላጆች ልጆችን መውለድ ቢፈልጉ ከጄኔቲክ ምክር አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ::

## ከሕመሙ ማገገምስ ይቻላል?

የዳንድይ ዎከር ሲንድሮም በአእምሮ እድገት ላይ የተለያየ ተጽእኖ ያሳድራል:: በአንዳንድ ህጻናት ላይ ትክክለኛ (ኖርማል) የሆነ ማስተዋል (ኮግኒሽን) ሲኖር በሌሎች ላይ ደግሞ የሀይድሮሴፋሉስ ህክምና ከተደረገ በኋላ እንኳን ከቶውኑ የተሟላ የአእምሮ እድገት እንዳይኖራቸው ያደርጋል:: ቤንደዚህ ሁኔታ ያሉ የህይወት ዘመን በሲንድሮሙ ክብደት እና ከዚያ ጋር ከተያያዙ መዛባቶች ይወሰናል:: ተደራራቢ የሆኑ ከጽንስ የሚጀምሩ መተጓጎሎች እድሜን ሊያሳጥሩ ይችላሉ::

## ምን አይነት ምርምር እየተደረገ ይገኛል?

በአሜሪካን የሚገኘው ብሔራዊ የኒዩሮሎጂካል ዲስኦርደር እና ስትሮክ ተቋም ውስብስብ የሆነውን የአእምሮ እድገት ሁኔታ የሚቃኙ ሰፋ ያሉ ምርምሮችን ያደርጋል እንዲሁም ይደግፋል:: ከእነዚህ መሰረታዊ ጥናቶች የሚገኘው እውቀት ስለ አንጎል መተጓጎሎች ለመረዳት ለሚደረገው ጥናት መሰረት ይጥላል እንዲሁም የዳንድይ ዎልከር ሲንድሮም እና ተመሳሳይ ለሆኑ የአንጎል መተጓጎሎች ለማከም እና ለመከላከል የሚሆኑ ተስፋን ሰጪ የሆኑ አዲስ የህክምና መፍትሔ ለመፈለግ ያስችላል::

## የዳንድይ ዎከር ሲንድሮም አሊያንስ (ሕብረት)ማን ነው አላማውስ ምንድን ነው?

ሕብረቱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በዳንድይ ዎልከር ሲንድሮም በተጎዱ ግለሰቦች የተቋቋመ ሲሆን ሁሉን አቀፍ ድርጅት ነው:: አላማውም የጋራ ጥያቄ በሆኑ ትምህርታዊ እና ጠቃሚ የመረጃ ልውውጦችን ለማድረግ እና በጽንስ የሚጀምር የአንጎል እክል (ዳንድይ ዎከር ሲንድሮም) ላይ ወገንተኛ ያልሆነ ምርምርን መደገፍ:: እንዲሁም የዳንድይ ዎከር ሲንድሮምን መንስኤ፣ ፈውስ እና ጉዳቱን ለማቅለል የሚረዱ ጥረቶችን ሁሉ እንደግፋለን:: በጉዳቱ ተጠቂ ለሆኑ ቤተሰቦች የምርምር ግኝቶችን በተደራጀ እና ቀላል በሆነ መልኩ በማቅረብ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ የትራንስሌሽናል ምርምር ውጤቶችን በማሰራጨት ውጤቶቹን በአፋጣኝ ከምርምር ገበታ ወደ በሽተኛው አልጋ በተፋጠነ መልኩ ማድረስ ይቻላል ብለን እናምናለን::